መብት እንዳላቸው ያመለከተ ሲሆን አንቀጽ 35/2/ም ቢሆን ሴቶች በጋብቻ ከወንዶች ጋራ እኩል መብት እንዳላቸው ተደንግጓል፡፡

በመሆኑም በጋብቻ ዘመን በተፈራ ንብረት ላይ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች እኩል መብት እንዳላቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡ ሆኖም ግን በተያዘው ጉዳይ ግራ ቀኙ ባደረጉት የጋብቻ ውል ተጠሪ ለአመልካች በዓመት ብር 120.00 እንደሚከፍላትና ከዚህ ውጭ አመልካ ንብረታቸው ላይ ምንም ዓይነት መብት እንዳይኖራት ያደረጉት ስምም የተጠቀሰውን የሕገመንግሥቱን የእኩልነት መብት ድንጋጌን የሚፃረር ነው፡፡ማንኛውም ሕግ ወይንም ልማዳዊ አሠራር ከሕገመንግሥቱ ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈፃሚነት እንደሌለው በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 9(1) ላይ ተመልክቷል፡፡

ከዚህም ሌላ አንድ የውል ግዴታ በሕግ አግባብነት ባልተቋቋመ ጊዜ በዚህ ውል መሠረት እንዲፈጽም ጥያቄ የቀረበለት ወገን ውሉ የማይረጋ ስለሆነ ተፈፃሚነት የለውም በማለት ይህንን ውል አልፈጽምም ማለት እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1809 የተመለከተ ሲሆን አመልካችም ከተጠሪ ጋር የተደረገው ውል ሕግን የሚፃረር ስለሆነ ተፈፃሚነት የለውም በማለት የተከራከሩ እንደመሆኑ መጠን በዚህ ስምምነት መሠረት ሊገደዱ የማይገባ ሆኖ ሣለ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤቶችን ውሣኔ በመሻር የአመልካችን የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 11110 ሐምሌ 3 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ከላይ እንደተጠቀሰው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካችና ተጠሪ ንብረት ሊካፈሉ ይገባል ተብሎ በጃቢ ጣህናን ወረዳ ፍ/ቤት በ14.4.99 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የምዕራብ ጎጃም ዞን ከ/ፍ/ቤት ይግባኙ አያስቀርብም በማለት በጥር 9 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በአግባቡ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት አጽንተነዋል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ





የሰ/መ/ቁ. 32130

መጋቢት 18 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ
መስፍን ዕቁበዮናስ
ሒሩት መለሠ
መድኀን ኪሮስ
አሊ መሐመድ

አመልካቾች፡- እነ እማዋይሽ ካሣ /6 ሰዎች/ ቀርበዋል፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አስቴር አህመድ - ጠበቃው ቀርቧል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ አባትነት እንዲታወቅ የቀረበን ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡

ተጠሪ በሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ እናታቸው በአመልካቾች ቤት በሠራተኛነት ተቀጥረው ሲሠሩ ከሟች አህመድ ይማም ጋር ከጋብቻ ውጪ በነበራቸው ግንኙነት የተወለዱ መሆኑና ሟችም ልጅነታቸውን ተቀብለው ሲረዱዋቸውና ሲንከባከቧቸው የነበረ በመሆኑ አባትነታቸው እንዲታወቅላቸው አመልክተዋል፡፡ አመልካቾችም ሟች ከእነርሱ በቀር ሌላ ልጅ የሌላቸው መሆኑን ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ተጠሪ ያቀረቡት ማስረጃ ልጅነታቸውን ለማወቅ የሚበቃ አይደለም በማለት ጥያቄያቸውን ውድቅ አድርጓል፡፡ ተጠሪ በውሣኔው ቅር በመሰኘት ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ይግባኙን

ያየው ፍ/ቤት የቀረበው ማስረጃ ሟች ተጠሪን በመንከባከብና በማስተማሩ ወይም በማሣደጉ ላይ እንደ አባት የተሣተፈ ለመሆኑ የሚያረጋግጥና ተጠሪ በሟች ስም ተመዝግበው በስሙ ትጠራ እንደነበር ተረጋግጧል በማለት ተጠሪ ከሟች አህመድ ይማም የተወለደች ልጅ ናት በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካቾች ቅሬታ በአጭሩ በአ/ብ/ክመ/ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 154/ሠ/ መሠረት አንድን ሰው አባት ብሎ ... ልጁን ለማስተማርና ለማሣደግ የሚያስፈልገውን እንክብካቤ ማድረጉ ... ንክብካቤ እና እርዳታ የተደረገው ተንከባካቢው ከወላጅነት ስሜት በመነጫ አኳኋን አባት ነኝ ከሚል እምነት የተነሣ መሆኑ መረጋገጥ ያስፈልገዋል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ሟች በርህራሄ እና ከሃይማኖታዊ ሥርዓት አፈፃፀም የተነሳ ተጠሪን ከመርዳት ውጪ ልጄ ናት ብሎ የረዳበት ጊዜ እንደሌለ ተረጋግጦ እያለ አባት ነው ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡

ይህ ትርጉም ተጠሪ የሟች አህመድ ይማም ልጅ መሆኗ ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት መረጋግጡን ለማጣራት የሰበር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ይገባል በማለቱ ተጠሪ ቀርበው መልስ ሠጥተዋል፡፡ በመልሳቸውም ሟች ተጠሪን እየተንከባከቡ ያሣደጉት በበጎ አድራጎት መንፈስ ሳይሆን የወለዷት ልጅ መሆንዋን በመግለጽ እንደሆነና ገንዘብ ይልኩላት የነበረውም በአባትነት መንፈስ መሆኑ ስለተረጋገጠ ውሣኔው ስህተት የለውም ብለዋል፡፡

ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው የተጠሪ ጥያቄ ሟች አቶ አህመድ ይማም አባታቸው መሆናቸው እንዲረጋገጥ የቀረበ ነው፡፡ የአ/ብ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሟች የተጠሪ አባት ናቸው የሚለው መደምደሚያ ላይ የደረሰው በክልሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 154/ሐ/ እና 154/ሠ/ መሠረት ሟች ተጠሪን በማሣደግ እንደአባት ተሣትፈዋል በማለት ነው፡፡ ፍ/ቤቱ ለውሣኔው መሠረት ያደረገው አንቀጽ 154/ሠ/ አባት ነው የተባለው ሰው ልጁን በመንከባከብ በማስተማር ወይም በማሣደጉ ላይ እንደ አባት በመሆን የተሣተፈ እንደሆነ አባት ተብሎ በፍርድ ሊወሰን ይችላል፡፡ ይህ የክልሉ ድንጋጌ ከፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ ምንም ልዩነት የሌለው መሆኑንም ተመልክተናል፡፡ በመሆኑም በዚህ ድንጋጌ አባት ነው ለመባል ሊረጋገጥ የሚገባው ፍሬ ነገር ምንድነው የሚለውን ማየቱ ጠቃሚ ነው? ድንጌጋው በግልጽ እንደሚያመለክተው አንድን ሰው አባት ነው ለማሠኘት ይኸው ሰው ልጁን ሲንከባከብ ሲያስተምር ወይም በማሣደጉ ሂደት ሲሣተፍ የነበረ መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ ነገር ግን እንክብካቤውንና እርዳታውን ማድረጉ በራሱ ሰውየውን አባት አያሠኘውም፡፡ ምክንያቱም ይህ እንክብካቤና እርዳታ ከርህራሔ እና ከሰብአዊነት ስሜት በመነጨም ሊደረግ የሚችል በመሆኑ ነው፡፡ ግለሰቡ አባት ነው ወደሚለው መደምደሚያ ለመድረስ ይህ እንክብካቤና እርዳታ አባት ነኝ ከሚል እምነትና ስሜት የመነጨና እንደ አባት በመሆን የተደረገ መሆኑም ጭምር ሊረጋገጥ ይገባዋል፡፡ ከዚህም በላይ እንክብካቤውን ሲያደረግ የነበረው ሰው ከእናትየው ጋር ልጅ ለመውለድ የሚያስችል ግንኙነት የነበራቸው መሆኑም ሊረጋገጥ የሚገባው ነው፡፡ በመሆኑም ከቀረበው ማስረጃ በእናትየውና አባት ነህ በሚባለው ሰው መሃከል ልጁን ለመካድ የሚያስችል ግንኙነት ሊኖር ይችላል የሚል እምነት የሚያሳድር ቅርበት መኖሩ እንዲሁም አባት ነህ የተባለው ሰው እርዳታውንና እንክብካቤውን ያደረገው እንደ አባት በመሆን መሆኑ ካልተረጋገጠ እርዳታ በማድረጉ ብቻ አባት ነው ወደሚለው መደምደሚያ መሄዱ የሕጉን አላማ የተከተለ አይደለም፡፡

በተያዘው ጉዳይ በሥር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ስንመለከት የተጠሪ እናት ከሟች እናትና አባት ቤት ተቀጥራ ስትሠራ ከሟች መውለዷን ሟች የነገራቸው መሆኑንና ሟች እንዳንዴ ገንዘብና ልብስ ይረዳት የነበረ መሆኑን በሚኒስትሪና በማትሪክ ካርዶች በሟች ስም ትጠራ የነበረ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ይህም ፍሬ ነገር ሟች ተጠሪ ልጄ ናት ብሎ ነግሮናል እንዲሁም አንዳንዴ ገንዘብ ይሰጣት ነበር ልብስም ያሠፋላት ነበር ከማለት ውጪ ይህንኑ